## በቶሮንቶ የተደረገው ስብሰባ ስሌቱና እውነቱ ይህ ነው - ከስብሰባው የነበረ

በመጀመሪያ በቅንጅት ስም ቶሮንቶ ላይ ስብሰባ የጠራው አንዳርጋቸው ጽጌ ያቂቂመው ተለጣፊው ቡድን ነው።

ኖቬምበር 1 ቀን ወይዘሮ ብርቱካንና አቶ ደበበ እሸቱ ይመጣሉና ባንዲራ ይዛችሁ እንድትመጡ ብለው ቢለፍፉም በአጠቃላይ አውሮፕላን ማረፊያ የተገኙት ጠቅላላ ሃያ ስድስት ሰዎች ሲሆኑ ከእነርሱም መካከል ጥቂቶቹ የእነብርቱካንን መቅረት ሲያውቁ ተናደው ጥለው ሲሄዱ ቀሪዎቹ 19 ሰዎች ብቻ ነበሩ አቶ ደበበን የተቀበሉ። ቀዝቃዛና ያው ልጆቻቸውን ሊጠይቁ የመጡ ሰው አቀባባል ነበር ማለት ይቻላል። የቶሮንቶ ሬዲዮ ፋና ወይም ሜዳልያ እና ኤሊያስ ክፍሌ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አቶ ደበበ እሸቱን ተቀበሏቸው ያሉት ፈጽሞ ውሸት ነው። አንዳንድ ወሬ አናፋሾች ድፍን ቶሮንቶ ወጥቶ ተቀበሏቸው ሲሉ አለማፈራቸው ያሳፍራል። እነወይዘሮ ብርቱካን ሀሙስ ቀኑ አርብ ማታ ይመጣሉ ተባለ። አርብ ማታም የነብርቱካን ድራሻቸው አልነበረም። አርብ ማታ ቶሮንቶ በሚገኝ ወያኔ የላከው የሬዲዮ ፋና ሰራተኛ በነበረው የአንዳርጋቸው ሬዲዮ ጣቢያ ለአቶ ደበበ ቃለመጠይቅ አድርጎ እግረ መንገዳቸውን ቅስቀሳ ሲያካሂዱበት ነበር። ኢንጂነር ግዛቸውም በሥራ ብዛት ወደ ቶሮንቶ መምጣት እንዳልቻሉና ወይዘሮ ብርቱካን እንደምትመጣ ገልጸዋል። እውነቱ ግን ኢንጂነር ግዛቸው አቶ ተስፋዬ ታሪኩ ባወጣባቸው ጉድ አፍረው ነው የቀሩት።

ቅዳሜ ኖቬምበር ሶስት ወይዘሮ ብርቱካን ስትገባ የተቀበሏት 17 ሰዎች ብቻ ነበሩ። በሰሜን አሜሪካ በጣም ቀዝቀዛና ለቅሶ ለመድረስ የመጣች የምትመስለው ቶሮንቶ ብቻ ነበር። የቫንኮቨሩ ከበደ ኃይለማርያም የባሕል ልብስ ለብሶ የሚታየው ፎቶ ለመነሳት ከቫንኮቨር በርሮ የመጣ ነበር። አቶ ደበበ እሸቱ ከኢትዮጵያ ሲገባ ያልተሰጠው እቅፍ አበባ ብርቱካን ስትመጣ ደርሷቸዋል። ሁለት ቀን ብቻ ነው ያስጠበቂቸው።

ኤልያስ ክፍሌ 700 ሰዎች በስብሰባው ተገኙ ያለውና 25 ሺህ ዶላር ተሰበሰበ ያለው የተለመደው የውሸት ፕሮፓጋንዳ ነው። እውነቱ እንዲህ ነው። እነርሱ እራሳቸው ከመግቢያ፣ ከጨረታ፣ ከፕሌጅና ካሽ ከሰጡ ሰዎች፣ ከአንዳንድ ነገሮች ሽያጭ በአጠቃላይ 20 ሺ 700 ብቻ ነው አገኘን ብለው የተናገሩት። ታዲያ ኤልያስ ክፍሌ 700 ሰው ስብሰባ ገባ ካለ የመግቢያው 30 ዶላር በ700 ሲባዛ 21000 ይሆናል። በካሽ በፕሌጅና በጨረታ የተገኘው ሲጨመርበት ሰላሳና እና ሰላሳ አምስት ሺህ በላይ ሊሆን ነው። እውነቱ ግን በአጠቃላይ በአዳራሹ የተገኙት እንግዶቹን ጨምሮ 259 ሰዎች ናቸው። በርከት ያሉት ብርቱካን ይቅርታ የጠየቀቻቸው ብሔረሰብ አባላትና የመግቢያ 30 ብር ይከፈልላችኋል ተብለው እየተከፈለላቸው የመጡና ሂዱ ተብለው የሄዱ የወያኔ ደጋፊዎች ሲሆኑ፣ አንዱ ይቅርታ የጠየቀችው የትግራይ ተወላጅ ብርቱካንን ሰማይ ጥግ አድርሷት የእቴጌ ጣይቱ ብጡልን ክብርና ዝና ለግሷት ምስጋና በምስጋና አድርጓታል። ያው የተለመደው የዘር ፖለቲካ በየሄደችበት መጫወቱን ቀጥላበታለች። የብርሃኑ ነጋም ሰዎችም እንዲወጡ በማህበራቸው ተነግሯቸዋል። ከወያኔ ንክኪ የሌለውና ጥያቄ ለመጠየቅ የሄደው ኢትዮጵያዊ ከ80 አይበልጥም። የነአየሎም ዘመዶች ባይረዱት ኖሮ ተለጣፊው ቡድን ከ50 በላይ ሰው አያገኝም ነበር ፍላየር ሲበትኑና፣ ወደ ስብሰባ ሂዱ እያሉ ቅስቀሳ ሲያደርጉ የነበሩ አበዛኞቹ የወያኔ ደጋፊዎች ነበሩ።

ተለጣፊውን ቡድን ሎጎውን እንዳይጠቀም ስለተከሰሰ እነርሱን ለማዳን አቶ ደበበ እሸቱ የቅንጅት ሎጎ የእኔ ነው። ለሁሉም የሰጠሁት እኔ ነኝ እና ማንም ሎጎው የእዙህ ድርጅት ነው ማለት አይችልም ብለዋል። እንዲያውም ጠበቃዬን አማክሬ ሎጎዬን ለማስመለስ እከሳለሁ በማለት እጅግ አስቂኝ አባባል ተናግረዋል። መልሱ አጭር ነው የቅንጅት ሎጎ የቅንጅት እንጂ የአቶ ደበበ አይደለም።

ወይዘሮ ብርቱካን ለተጠየቀችው ጥያቄ ስትመልስ ቀድሞ ሲረዳ የነበረውን የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት በቶሮንቶን አናግረን ነበር ምንም ምክንያት ሳይናገር አትምጡ አለን በማለት ሽምጥጥ አድርጋ ዋሽታለች። እውነቱ ግን በክብር አገር ቤት እያለች ለተጻፈላት ደብዳቤ መልስ አለመስጠትዋ እና ከመጀመሪያውኑ ከተለጣፊው ቡድን ጋር መወገኗ የታወቀ ነው። የጻፉላትን ግልጽ ደብዳቤ እንደገና ታንበው።

በአጠቃላይ ስብሰባው የወያኔ ደጋፊዎችን በማስተባበር በውስጥ ቅስቀሳ ለመምጣታቸው ከመጡት መካከል 200 የሚሆኑት ላለፉት ረጂም ዓመታት በየትኛውም የጸረ ወያኔ እንቅስቃሴ መጥተው የማያውቁ፣ አገር ቤት የሚመላለሱና ቦታ የተመሩ፣ የተቃዋሚውን ክፍል ሲያዳክሙና አፍራሽ ቅስቀሳ ሲያደርጉ የነበሩ ናቸው። እነ ወይዘሮ ብርቱካን አውቀውበታል ከወያኔ ጋር ኑሮ። አዬ ቅሌት !